# የሞኖክሎናል አንቲቦዲ ህክምናዎች ምንድን ናቸው?

የከባድ የ COVID-19 ህመም ስጋት ካለብዎት እና ለ COVID-19 ፖዘቲቭ የምርመራ ውጤት ካልዎት ወይም ፖዘቲቭ የምርመራ ውጤት ካለው ሰው ጋር የቅርብ ንክኪ ከነበርዎት፣ የሞኖክሎናል አንቲቦዲ (mAb) ህክምናን ከግምት ውስጥ ሊያስገቡ ይችላሉ። እድሜዎን፣ የጤና ታሪክዎን፣ እና ለምን ያክል ጊዜ ምልክቶች እንደነበርዎት መሰረት በማድረግ COVID-19 ን ለማከም ለ mAb ህክምና ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።

የ mAb ህክምና COVID-19 የሚያስከትለውን ቫይረስ ሰውነትዎ ውስጥ ወዳሉ ህዋሳት እንዳይገባ ሊከለክል እንዲሁም በሰውነትዎ ውስጥ ያለውን የቫይረስ መጠን ሊገድብ ይችላል። ይህም ማለት ዝቅተኛ ምልክቶች ሊኖርዎት ይችላል እንዲሁም በሆስፒታል ውስጥ የመቆየት አስፈላጊነትን ሊቀንስ ይችላል።

የ mAb ህክምና የሚከተሉትን ሰዎች ሊረዳ ይችላል፦

- በጣም ከባድ በሆኑ ምልክቶች የመታመም ከፍተኛ እድል ያላቸው ሰዎች **እና**
- ከ COVID-19 ፖዘቲቭ የምርመራ ውጤት ጋር ለ 7 ቀናት ወይም ከዚያ ላነሰ ጊዜ የቆዩ ምልክቶች ያሏቸው ሰዎች **ወይም**
- በቅርቡ ፖዘቲቭ የምርመራ ውጤት ያለው ሰው ጋር የቅርብ ንክኪ የነበራቸው ሰዎች

## ሞኖክሎናል አንቲቦዲ ምንድን ነው?

ሰውነትዎ በተፈጥሮ በሽታን ለመከላከል አንቲቦዲዎችን ይሰራል። ሆኖም፣ ሰውነትዎ SARS-CoV-2 ን፣ COVID-19 ን የሚያስከትለው ቫይረስ፣ የሚመስል ኖቬል (ወይም አዲስ) ቫይረስን ለማወቅ የተዘጋጀ አንቲቦዲ ላይኖረው ይችላል። ሞኖክሎናል አንቲቦዲዎች፣ ወይም mAbs፣ ልዩ ኢንፌክሽንን (በዚህ ሁኔታ፣ SARS-CoV-2 ማለት ነው) ለመዋጋት በላብራቶሪ ውስጥ ይሰራሉ እንዲሁም በኢንፊዩዥን (በመርፌ) መልክ በቀጥታ ይሰጡዎታል። የ mAb ህክምና ለከባድ ምልክቶች ወይም በሆስፒታል ውስጥ ለመቆየት ከፍተኛ እድል ካልዎት ሊረዳ ይችላል።

የ COVID-19 የ mAb ህክምና ከ COVID-19 ክትባት የተለየ ነው። ክትባቱ የሰውነትዎን ተፈጥሯዊ በሽታ የመከላከል ግብረ መልስ ያነሳሳዋል፣ ነገር ግን ቫይረሱን ለመከላከል በቂ አንቲቦዲዎችን ለማምረት ግን ሳምንታትን ሊወስድ ይችላል። ስለዚህ፣ ቫይረሱ ካለብዎት፣ የ mAb ህክምና ለሰውነትዎ ራሱን ለመከላከል የሚያስችሉትን አንቲቦዲዎች ይሰጠዋል። የ mAb ህክምና ከክትባቱ የሚገኘውን በሽታ የመከላከል አቅም አይተካም ነገር ግን በከባድ የ COVID-19 በሽታ ለመያዝ ዕድል ካልዎት ሊረዳዎ ይችላል።

## የሞኖክሎናል አንቲቦዲ ህክምና ሊያሳምመኝ ይችላል?

የአንቲቦዲ ህክምናዎች ማንኛውንም ህይወት ያለውን ቫይረስ አይዙም፣ ስለዚህ ከ mAb ህክምና በ COVID-19 የመያዝ ምንም አይነት ዕድል የልዎትም። ሆኖም ግን፣ የአንቲቦዲው ህክምና የጎንዮሽ ጉዳቶች ሊኖሩት ይችላል። ሊከሰቱ ስለሚችሉ የጎንዮሽ ጉዳቶች እና ካጋጠምዎት ምን ማድረግ እንዳለብዎት እባክዎ ከጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ጋር ይነጋገሩ።

## • ለሞኖክሎናል አንቲቦዲ ህክምና ብቁ ካልሆንኩኝስ?

የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ለ mAb ህክምና ብቁ እንዳልሆኑ ሊወስን ይችላል። ለዚህ ብዙ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ። ሁሉንም የብቁነት መስፈርት ላያሟሉ ይችላሉ፣ ወይም ለ mAb ህክምና ብቁ እንዳይሆኑ ያደረግዎት ስር የሰደደ የጤና ሁኔታ ሊኖርዎት ይችላል። ለሌሎች የህክምና አማራጮች የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎን ይጠይቁ።

## • የሞኖክሎናል አንቲቦዲዎችን እንዴት ማግኘት እችላለሁ?

ደረጃ 1፦ የ COVID-19 ፖዘቲቭ የምርመራ ውጤት ይኑርዎት እንዲሁም ምልክቶች ለ 7 ቀናት ወይም ከዚያ ላነሰ ጊዜ ይኑርዎት።

ደረጃ 2፦ ከጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ሪፈራል ያግኙ።

ደረጃ 3፦ ሊገኝ የሚችል የፊዩዥን ማዕከል ያግኙ።

mAb ን ለማግኘት በጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ለህክምና መላክ እንዲሁም ሊገኝ ወደሚችል የኢንፊዩዥን ማዕከል መመራት አለብዎት። **የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ከሌልዎት፣** ስለ ምልክቶችዎ እና ህክምናዎ ማንን ማነጋገር እንዳለብዎት ለማወቅ ወደ Combat COVID Monoclonal Antibodies Call Center (ኮምባት ኮቪድ የሞኖክሎናል አንቲቦዲዎች የጥሪ ማዕከል) በ 1-877-332-6585 ይደውሉ።

Washington State Department of Health

DOH 825-031 March 2022 Amharic

ይህን ሰነድ በሌላ ቅርጸት ለመጠየቅ፣ 1-800-525-0127 ላይ ይደውሉ። መስማት ለተሳናቸው ወይም መስማት ለሚቸገሩ ደንበኞች፣ እባክዎ በስልክ ቁጥር 711 (Washington Relay) ይደውሉ ወይም ወደ mailto:ecivil.rights@doh.wa.gov ኢሜይል ይላኩ።